**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

4ki Diro Kiiro 32

Hawaasa, Bocaasa 26/ 2016 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፬ኛ ዓመት ቁጥር ፴፪

ሀዋሳ፣ ኅዳር ፳፮ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም

## Amado

**Wodhote Kiiro 32 /2016**

**Yirgaalamete Hosipitaale Xagishshu Kolleejje Uurrisate, Biilloonyenna Loossa Murate Fultino Wodho … Qoola**

## **Wodhote Kiiro. 32 /2016**

## **Yirgaalamete Hosipitaale Xagishshu Kolleejje Uurrisate, Biilloonyenna Loossa Murate Fultino Wodho**

Dhibba gargarate aana safantino gobbanke fayyimmate poolise loosu aana hosiisate dagoomu keeraanchimma qara qarra ikkitinore taraabbannore ikkitinonna ikkitinokki dhibba gargara dandiitannore uurrinshaamo dhukanna ikkadimma lossate hasiisannoha ikke leellinohura,

Gobbankerano ikko qoqqowinkera dagankeha fayyimmate qarra gatisatenna konni ledo amadame nooha jawa fayyimmate ogeeyye roorinni xaphooma xagisaanonna ispeeshaaliste xagisaano xe’ne wonshate safote hedonna looso illachishino qajeelsha

## ማውጫ

**ደንብ ቁጥር.፴፪/፳፻፲፮**

**ይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ …ገጽ**

## **ደንብ ቁጥር ፴፪ /፳፻፲፮**

## **ይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ**

በሽታን በመከላከል ላይ የተመሠረተውን የሀገራችን የጤና ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የህብረተሰቡ የጤና ዋንኛ ችግሮች የሆኑትን ተላላፊ የሆኑና ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እንዲያስችል ተቋማዊ አቅምና ሙያዊ ብቃትን ማሳደግ አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

በሀገራችንም ሆነ በክልላችን የህዝባችንን የጤና ችግር ለመቅረፍና ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለውን የከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች በተለይም ጠቅላላ ሐኪሞችንና ስፔሻሊስት ሐኪሞች እጥረትን ለመቅረፍ የንድፈ-ሀሳብና ተግባር ተኮር



AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

qineessate hospitaalete mereershimmanni rosonna qajeelsha hattonno fayyimmate owaante karse loosannoha ikke ikkado dandoonna silanchimma noonsa qaddo fayyimmate ogeeyye burqissanno fayyimmate sayinse qajeelsha uurrisa hasiissinnota ikkite leeltinohura,

Owaatamaano illachishino silanchimmasi agadhinonna jiro garunni horoonsi'ra dandiissitanno ikkito kalaqatenni konni albaanni lame uurrinsha babbaxxite fayyimmate hajora loossanni nooti Yirgaalamete Hospitaalenna Yirgaalamete Xagishshu Fayyimmate Sayinse Kolleejje gobbate fayyimmate poolise loosu aana hosiisate kaa'litannotanna fayyimmate handaarira hasi'noonni soorro borrreessiisate dandiissanno garinni mitte uurrinshawa qole karsatenni woyyinohanna qinaawinoha baalanka hanqafinno owaante uynanni gede haaru garinni tantana hasiissinohura,

Aliidi rosu lallawi kiiro 1152/2011 quwa 58 (1) seeroonni garinninna Qoqqowu Bayiriidi Seeri Quwa 57 (6) garinni Gashshootu Amaale Mini tenne wodho fushshino.

## GAFA MITE
## XAPHOOMA WORO

1. **Harancho Umo**

   Tini wodho "**Yirgaalamete Hosipitaale Meedikaalete Kolleejje Uurrisatenna Biilloonyenna Looso Murate Fultino Wodho Kiiro…/2016**" yne xawinsara dandiinanni.

2. **Tiro**

   Konni lallawi giddo qaalu eo wole tiro uysiissannoha ikka hoogguro:-

ስልጠናን በማቀናጀት በሆስፒታል ማዕከልነት ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የጤና አገልግሎት አዋህዶ የሚሰራ ሆኖ በቂ ችሎታና ጥራት ያላቸውን ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎችን የሚያመርት እራሱን የቻለ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ተገልጋይ ተኮር የሆነ ጥራቱን የጠበቀና ሀብትን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል ሁኔታ በመፍጠር ከዚህ በፊት በሁለት ተቋማት ተለያይተው በጤና ጉዳይ ሲሰሩ የነበሩት የይርጋዓለም ሆስፒታል እና የይርጋዓለም ህክምና ኮሌጅ የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ በሚረዳና በጤናው ዘርፍ የተፈለገውን ለውጥ ለማስመዝገብ በሚያስችል መልኩ ወደ አንድ ተቋም በማዋኸድ የተሻለና የተቀናጀ ሁለንተናዊ አገልግሎት እንዲሰጥ በአዲስ መልኩ ማደራጀት በማስፈለጉ፣

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 58 (1) በተደነገገው መሠረት እና በክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 57 (6) መሰረት መስተዳድር ምክር ቤቱ ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "**ይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር** …. /2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1) “**qoqqowo**” yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti;
2) “**biiro**” yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Fayyimmate Biirooti;
3) **’’biirote Sooreessa’’** yaa qoqqowu fayyimmate biiro sooreessaati;
4) “**xagishshu Kolleejje**” yaa Yirgaalamete Hospitaale Xagishshu Kolleejjeeti;
5) “**ministere**” yaa garimmasi garinni Tophiyu Federaalete Demokirasitte Ripaabilike Fayyimmate Ministerenna Rosu Ministereeti.
6) **“lallawa”** yaa aliidi rosu lallawi kiiro 1152/2011.
7) **“manajimente”** yaa xagishshu kolleeje hajubba gumulate biilloonye uynoonnisi bisooti;
8) “**qara dayirekitere**” yaa tenne wodho kaiminni biilloonsinoonnihu/sommoonni xagishshu kolleejje aliidi sooreessaati;
9) **“aantano qara dayrekitoreetoota”** yaa tenne wodho garinni somaminnoha ikke xagishshu kolleejjera aantancho qara dayirekiterimanni gaamantino handaara massagannoreeti;
10) **“akadamikete dagooma”** yaa xagishshu kolleejje giddo uurrinshatenni woy yannate geeshsha rosatenni, rosiisatenninna xiinxawote assoota aana bobbahe afamanno mannoota hanqafinoho;
11) **“akadamikete loosaasincho’’** yaa xagishshu kolleejje baalate rosiisate woy xiinxallote hajubba massagannohonna yawo uynoonnisi bisooti;
12) “**gashshootu irko aanno loosaasincho**” yaa gashshootu, gatamarshu, agarooshshunna keeraanchimmate woy labbeemme loossa

1) **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፣
2) **“ቢሮ”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ፣ መንግስት ጤና ቢሮ ነው፣
3) **“የቢሮ ኃላፊ”** ማለት የክልሉ ጤና ቢሮ ኃላፊ ነው፣
4) **“የህክምና ኮሌጅ”** ማለት ይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ ነው፣
5) **“ሚኒስቴር”** ማለት እንደየአግባብነቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጤና ሚኒስቴር እና ትምህርት ሚኒስቴር ነው፣
6) **“አዋጅ”** ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 ነው፣
7) **“ማኔጅመንት”** ማለት በህክምና ኮሌጁ ጉዳዮች ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፣
8) **“ዋና ዳይሬክተር”** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰየመ የህክምና ኮሌጁ የበላይ ኃላፊ ነው፣
9) **“ም/ዋና ዳይሬክተሮች”** ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተሰየሙ ሆነው በህክምና ኮሌጁ በምክትል ዋና ዳይሬክተርነት የተመደቡበትን ዘርፍ የሚመሩ ናቸው፣
10) **“የአካዳሚክ ማህበረሰብ”** ማለት በየህክምና ኮሌጁ ውስጥ በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት በመማር፣ በማስተማር እና በምርምር ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎችን ያቀፈ ነው፣
11) **“የአካዳሚክ ሰራተኛ”** ማለት በህክምና ኮሌጁ በማስተማር ወይም የምርምር ጉዳዮችን የሚመራና ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፣
12) **“የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ”** ማለት የአስተዳደር፣ የጥገና፣ የጥበቃና ደህንነት ወይም የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከናውን የህክምና ኮሌጁ ሠራተኛ ነው፣

loosanno xagishshu kolleejje loosaasinchooti;

13) "**borde**" yaa tenne wodho quwa (16) garinni sommonni xagishshu kolleejje massagaano Bordeeti.
14) **"senete"** yaa xagishshu kolleejje akadamikete handaara aana goofimarchu gumulo aanno bisooti;
15) "**akkadaamikete Komishiine**" yaa tenne wodho quwa (33) garinni uurritinnote.
16) **"ogeessa"** yaa babbaxxitinno xagishshu oggimmanni qajeeltinnonna oggimmansanni owaante uytannoreeti.
17) **"rosaanno"** yaa ayno xagishshu kolleejera rosantinnonna wolootu akadamikete piroogiraamubbara rosate eate safaraancho wonshe borreesaminoho;
18) **''gidooyidi Eo''** ya xagishshu kolleejje sokkase gumulate harinshora loossanno xaaddinno loosate millimilonni gamba assitanno uduunnu woy owaantete baatoosheti;
19) "**Mancho**" yaa kalaqamu woy seerunni mannimmate qoosso uyiinoonnisi bisooti yaate;
20) Tenne wodho giddo mitte kooteemmanni xawinsoonnihu wole kooteemmano hanqanfannoho.

## 3. Uurrisa

Yirgaalamete Hosipitaale Xagishshu Kolleejje konni gedenoonni "Xagishshu Kolleejje" ynanni woshshinanni jefisiisaanote bissa biilloonyenna looso murate fulino lallawi kiiro 32/2015 qoqqowu fayymate biirora uynoonnisi biilloonyi garinni xagishshu owaantenna aliidi rosu lallawi kiiro 1152/2011 garinni aliidi xagishshu qajeelsha uytannota ikkite seeru bisi noosi aliidi xagishshunna rosu uurrinsha ikkatenni tenne wodhonni uurritinno.

13) **"ቦርድ"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ (16) መሠረት የተሰየመ የህክምና ኮሌጁ አመራር ቦርድ ነው፣
14) **"ሴኔት"** ማለት በህክምና ኮሌጁ የአካዳሚክ ዘርፉን በበላይነት የሚመራና በአካዳሚክ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው፣
15) **"አካዳሚክ ኮሚሽን"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ (33) መሠረት የተቋቋመ ነው፣
16) **"ባለሙያ"** ማለት በተለያዩ የህክምና ሙያ መስኮች የሰለጠኑና በሙያቸው አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፣
17) **"ተማሪዎች"** ማለት ማንኛውም በህክምና ኮሌጁ በመደበኛና ሌሎች የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ለመማር የመግቢያ መስፈርቱን አሟልቶ የተመዘገበ ነው፣
18) **"የውስጥ ገቢ"** ማለት የህክምና ኮሌጁ ተልዕኮዎቹን በማሳካት ሂደት ከሚያከናውናቸው ተጓዳኝ የሆኑ የስራ እንቅስቃሴዎች የሚሰበስበው የእቃ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ነው፣
19) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
20) በዚህ ደንብ ውስጥ በአንድ ፆታ የተገለፀው ሌላኛውንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. መቋቋም

ይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ ከዚህ በኋላ "የህክምና ኮሌጅ" እየተባለ የሚጠራ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 32/2015 ለክልሉ ጤና ቢሮ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የህክምና አገልሎት እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 መሠረት የከፍተኛ ሕክምና ስልጠና የሚሰጥ ሆኖ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የከፍተኛ የህክምናና ትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

4. **Hundaanchimma**

Xagishshu Kolleejje garimmasi garinninna garimma noonsa gobbate seeri garinni rosu ministerenna fayyimmate ministere ledo heedhannose loosu xaadooshshi noo gedeenni heedheenna hundaanchimma qoqqowu fayyimmate biiroraati.

5. **Xagishshu Kolleejje Uurrinsha**

1) Massagote Borde, seenete, qara dayirektere, aantano qara dayrekitoreetotinna akkadaamikete komishiine, diinenna aantano diinoota,
2) Akkadaamikete loosaasine.
3) Gashshootunna irko uytanno loosaasine

6. **Hexxo**

Xagishshu Kolleejjera aantanno hexxo heedhannose:-

1) Safote hedonna leellino qajeelsha karsinno rosu amuraate diriirsate addinni pirogiramubba fayymmate ogimma rosi qajeelsha aatenni ikkadonna dancha akattanni ragantino fayymmate ogeeyye latisate.
2) Dagoomaho fayyimmate qarri aana illachishshino rosu amanyooti ledo quwantino fayyimmate owaante aate.
3) Rosunni afidhino egenno loosunni afidhino rosichi ledo waaxatenni dagoomaho fayyimmate owaante uytanni lekkisaanchonna silanchimma noonsa fayyimmate ogeeyye rosiissanno ikkadda rosiisaano latiqisate.
4) Qoqqowunnino sae gobbate jajjabba xagishshu ogeeyye anje tirate dandiisanno garinni egennotenni, dandootenninna danchu akatinni bilchaatino jajjabba xagishshu ogeeyye qajeelsatenni ikkado mannu wolqa kalaqate.
5) Garimmate rosatenna rosiisate amanyoote

4. **ተጠሪነት**

የህክምና ኮሌጁ እንደየአግባብነቱና አግባብ ባላቸው የሀገሪቱ ሕግ መሠረት ከትምህርት ሚኒስቴርና ጤና ሚኒስቴር ጋር የሚኖረው የሥራ ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ጤና ቢሮ ነው፡፡

5. **የህክምና ኮሌጁ አቋም**

1) የአመራር ቦርድ፣ ሰኔት፣ ማኔጅመንት ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና አካዳሚክ ኮሚሽን፣ ዲንና ምክትል ዲኖች
2) የአካዳሚክ ሠራተኞች
3) የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች

6. **ዓላማ**

የህክምና ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) ንድፈ ሃሳብንና ተግባራዊ ስልጠናን ያዋሃደ የትምህርት ሥርዓትን በመዘርጋት በተለያየ መርሀ-ግብሮች የጤና ባለሙያነት ትምህርት ስልጠና በመስጠት ብቁና መልካም ሥነ-ምግባርን የተላበሱ የጤና ባለሙያዎችን ማፍራት ነው፡፡
2) በህበረተሰቡ የጤና ችግር ላይ የተመረኮዘና ከትምህርት ሥርዓቱ ጋር የተጣጣመ የጤና አገልግሎት መስጠት ነው፡፡
3) በትምህርት ያገኙትን እውቀት በሥራቸው ካገኙት ልምድ ጋር በማጣመር ለህብረተሰቡ የህክምና አገልግሎት እየሰጡ ተተኪና ጥራት ያላቸውን የጤና ባለሙያዎች የሚያስተምሩ ብቁ መምህራንን ማፍራት ነው፡፡
4) የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን የከፍተኛ ሕክምና ባለሙያዎች እጥረት ለመፍታት በሚያስችል መልኩ በእውቀት፣ ክህሎትና በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፁ የከፍተኛ ሕክምና ባለሙያዎች በማሰልጠን በቂ የሰው ኃይል ማፍራት፣
5) ተገቢውን የመማር ማስተማር ሥርዓት

qixxeessatenni illacha tunganni fayyimmate hajubba aana qarra tirtannonna loosu aana hossanno xiinxallo assanna loosu aana hosiisa.

6) Gobbate fayyimmate hasatto aana safantino illachisi egennotenna tekinoloojete taraawo aana ikkitinno xiinxallo harisanna bowirsa.
7) Gobba kalqete deerrinni heewisamaancho ikkitanno gede dandiisiissannose, silanchimmase agadhitinnonna gobbate horo noonsata fayyimmate egennaamma dagooma kalaqatenni lawishshanna bilchaata ikkino assootta jeefate.

7. **Xagishshu Kolleejje Xagishshunna Akkadaamikete Wolapho**

1) Xagishshu kolleejje hexxose jeefisate gobbate giddo noo seeri garinni wolambinatu hee'rannose.
2) Uytanno baalanka hanqafinno xagishshu owaante aana wolapho heedhannose.
3) Xagishshu kolleejje wolapho agarsiissanno yannara dagoomittete qeechi budeno bowiranno gede assa heedhannose.
4) Xagishshu kolleejje tenne wodhonninna gara ikkino gobbate seerubbanni hattono kalqete danchu rosichi garinni ogimmate wolapho garunni massagantanno gede assa noose.

8. **Rosu Pirogiraame**

1) Xagishshu kolleejje rosu pirogiraame.
   a. Xaaddotenni
   b. Fooliishshote barrubba hattono
2) Ikkadimmatenni woyyaawa noonsa handaarubbara egennonna ogimma saysate harancho yanna qajeelsha uytara dandiitanno. Tittirshu garimma noo seerinni gumulamanno.

በመዘርጋት ትኩረት በሚሹ የጤና ጉዳዮች ላይ ችግር ፈቺና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ምርምሮችን ማካሄድና ማስረጽ፤

6) በአገሪቱ የጤና ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ትኩረቱ በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የሆነ ምርምርን ማራመድና ማጐልበት፤
7) አገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችሏትን፣ ጥራቱን የጠበቀና ሀገራዊ ፋይዳ ያለውን የጤና አካዳሚክ ማህበረሰብ በመፍጠር በአርአያነት ተጠቃሽ የሆነ ተግባራትን መፈፀም፤

7. **የህክምና ኮሌጁ የህክምና እና አካዳሚያዊ ነፃነት**

1) የህክምና ኮሌጁ ዓላማውን ለማሳካት በሀገሪቱ ባለው ሕግ መሠረት አካዳሚያዊ ነፃነት ይኖረዋል፡፡
2) በሚሰጠው ሁሉን አቀፍ የክህምና አገልግሎት ላይ ሙሉ ነፃነት ይኖረዋል፡፡
3) የህክምና ኮሌጁ አካዳሚያዊ ነፃነቱን ሲያራምድ የማህበራዊ ኃላፊነት ባህልን እንዲበለጽግ ማድረግ ይኖርበታል፣
4) የህክምና ኮሌጁ በዚህ ደንብና አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጐች እንዲሁም በዓለም አቀፍ መልካም ልምድ መሠረት የአካዳሚያዊ ነፃነት አተገባበር በሥርዓት እንዲመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8. **የትምህርት መረሃ-ግብር**

1) የህክምና ኮሌጁ የትምህርት መረሃ-ግብር
   ሀ/ በመደበኛ
   ለ/ በእረፍት ቀናት እንዲሁም
2) በብቃት ማሻሻያ አስፈላጊነት በሚኖራቸው መስኮች እውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን ሊሰጥ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ አግባብነት ባለው ህግ ይወሰናል፡፡

**9. Rosu Budi Amado**

Xagishshu kolleejje rosu budi suudishsha, loossanna keenote hexxo rosaanchu hasiissannota saynsete egenno, cu'misiissannotanna wolaphotenni wodancha jawaachishshannota ikka noose.

**10. Akkadaamikete Diro**

Xagishshu kolleejje qajeelsitanno akadamikete diri ministere wortino akadamikete diro ikkanno.

**GAFA LAME**

**Tantano, Biilloonyenna Looso**

**11. Tantano**

1) Borde
2) Manajimente
3) Senete
4) Qara Dayrektere
5) Aantaano Qara Dayrekitoreetooti
6) Akkadaamikete Komishiine

**12. Xagishshu Kolleejjete Loosonna Biilloonye**

Xagishshu kolleejje aantanno loossanna biilloonyi hee'rannose:

1) Xagishshu amuraate loossanna gumaanchimma harunsanna buuxa.
2) Xagishshu owaante aamanshi aanti gedeno amanyoote harunsse loosa.
3) Taraawannonna taraawannokki dhibba gargarate dandiissitanno harinsho suudisatenni loosu aana hosiisa.
4) Hedeweelcho xisso xagishshu owaante aanna owaantete aana hasiissanno woyyeesso assa.
5) Dagoomu owaante xagishshunni, xiinxallotenna rosu loossa ledo xaaddenna sumuu yite loossanno injo kalaqa

**9. የሥርዓተ ትምህርት ይዘት**

የህክምና ኮሌጁ የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣ ትግበራና የምዘና ዓላማ፣ ተማሪው ተገቢው ሳይንሳዊና ተግባራዊ ክህሎት የሚያስጨብጥ እና በነፃነት፣ ማሰብን የሚያበረታታ፣ መሆን ይኖርበታል፡፡

**10. የአካዳሚክ ዘመን**

የህክምና ኮሌጁ የአካዳሚክ ዘመን በሚኒስቴሩ በተቀመጠው የአካዳሚክ ዘመን ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር**

**11. አደረጃጀት**

1) ቦርድ
2) ማኔጅመንት
3) ሴኔት
4) ዋና ዳይሬክተር
5) ም/ዋና ዳይሬክሮች
6) አካዳሚክ ኮሚሽን

**12. የህክምና ኮሌጁ ሥልጣንና ተግባር**

የህክምና ኮሌጁ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1) የህክምና ስርዓት አተገባበርን፣ ዉጤታማነትን፣ የመከታተልና የማረጋገጥ
2) የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ቅደም ተከተል ስርዓቱን ተከትሎ የማከናወን፣
3) ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ፣
4) የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መስጠት እና በአገልግሎቱ ላይ ተገቢዉን ማሻሻያዎች የማድረግ
5) የማህበረሰብ አገልግሎት ከህክምና፤ ከምርምር እና ትምህርት ስራዎች ጋር ተጣጥመዉ እና ተናበዉ እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር

6) Yannillincho ikkitino xagishshu udiinne horoonsi’ratenni silanchimma noota xagishshu owaante aa
7) Baxxino illacha assatenni qaaqquullunna ilino amuwira (MCH) xagishshi owaantenna roso aa
8) Illete xagishshira hasiissanno udiinnu eo wonshanna illete xagishshi owaante aa
9) Surrete xissamaanora baxxino illacha assatenni xagisate owaante aa
10) Xagishshu kolleejje deerra quwaminoha xaphooma dare gowate xagishshi kifile qixxeessatenni xaphooma dare gowate owaante aa
11) Miqqichcho darre xaggisa kaajinonna hasiisanno shiqqo wonshatenni owaante aa
12) Paatoloojete xagishshanna fajjiniro rosu owaante aa.
13) Giddo dhibbi xaggishshanna roso wo’minno garinni aa
14) Hasiisanno shiqqo wonshatenni mule hayshate xagishshu owaante aa
15) Xagishshu kolleejjera uynnanni loossara hasiissanno yannillaancho xagishshu rosi udiinne qoleno ikkadda mannu wolqanni wonsha
16) Ministere fushshitanno filate safaranonna biddissi garinni rosaano adha
17) Qoqqowunniha jawiidi fayyimmate ogeeyye hasatto kaima assatenni bilchaata qajeeltino xagisaano batinyunninna silanchimmatenni qixxeessa
18) Gobboomu keeno kaima assinoha rosu qajeelshi pirogiraame qineessatenni Borde gumultanno woyte loosu aana hosiisa
19) garimmasi garinni rosu pirogiraamubbanni qajeelatenninna hasiisannoha rosaanote keeno

6) ዘመናዊ የሆኑ የህክምና መሳሪያዎችን በመጠቀም ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት መስጠት፣
7) የተለየ ትኩረት በማድረግ ለህፃናት እንዲሁም ለወላድ እናቶች (MCH) የህክምና አገልግሎት እና ትምህርት መስጠት
8) ለአይን ህክምና የሚያስፈልጉ ግብኣቶችን ማሟላት እና የዓይን ህክምና አገልግሎት መስጠት
9) ለአእምሮ ህሙማን ልዩ ትኩረት በማድረግ የህክምና አገልግሎት መስጠት
10) የህክምና ኮሌጁን ደረጃ የሚመጥን የጠቅላላ ቀዶ ህክምና ክፍል በማደራጀት የጠቅላላ ቀዶ ህክምና አገልግሎትና ትምህርት የመስጠት
11) የአጥንት ቀዶ ህክምና በተጠናከረና አስፈላጊዉን ግብአት በማሟላት አገልግሎት መስጠት
12) የፓቶሎጂ ህክምና እና ሲፈቀድም የትምህርት አገልግሎት መስጠት.
13) የውስጥ ደዌ ህክምናና ትምህርት በተሟላ መልኩ መስጠት
14) አስፈላጊውን ግብኣቶች በማሟላት የኩላሊት እጥበት ህክምና አገልግሎት መስጠት
15) በህክምና ኮሌጁ ለሚሰጡ ተግባራት አስፈላጊ የሆኑና ዘመናዊ የህክምና የትምህርት ግብዓቶች እንዲሁም በበቂ የሰው ሀይል ማሟላት
16) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የምልመላ መስፈርትና መመሪያ መሠረት ተማሪዎችን መቀበል፤
17) የክልሉን የከፍተኛ ሕክምና ባለሙያ ፍላጐት መሠረት በማድረግ ብቃት ያላቸውን የሰለጠኑ ሐኪሞች በብዛትና በጥራት የማፍራት፤
18) አገር አቀፍ መለኪያዎችን መሠረት ያደረገ የትምህርትና ስልጠና መረሃ-ግብር በመቀየስ ቦርዱ ሲያፀድቅለት በሥራ ላይ ማዋል፤
19) እንደአግባብነቱ በትምህርት ፕሮግራሞች በማሰልጠንና ተገቢውን የተማሪዎች ምዘና

assatenni hansoonni guma borreessissinno qajeelaanora hasiisannoha rosu tajensa digiretenni, masitersetenni dokitereetete digirenni aa

20) garimmasi garinni babbaxxino qajeelshu, xiinxallotenna xiinxaawote gola uurrisanna jawaachisha

21) Rosunna xagishshu owaantera horo noose irkote uduunenna maxaaffa attamanna tantana

22) Gobbate gobbaanni afantanno labbanno yuniversitubbanna xagishshu uurrinshuubba ledo xadooshshe kalaqatenna xagishshu tekinoloojubbanna uduunne hidhatennino ikko kaa’lotenni afamanno gede assatenni kolleejjete xuka lossa

23) Baxxino illachu raga hasidhanno fayymmate handaarra biirote woy mootimmatenni hansiro baxxitino pirogiraamenni haranchotenna mereerimu deerri qajeelshuwa qixxeessatenninna loosatenni seertifikeetetenna dippoloomu taje aa

24) Xagishshu kolleejje loosaasinenna rosaano afidhanno xagisi’rate owaante Borde fushshitanno biddissi kaiminni baatooshshe jeefa.

25) Fayyimmate ledo amadantino rosu taje elektirooniksetenna attamote midiyra woy yannillincho xaadooshshu hayyo horoonsi’re tuqisatenni,

26) Rosaanote rosu fulo baatooshshe, owaantete baatooshshenna woleno babbaxxitino buenni gamba assinanni eo garunni gamba assa fayynaansete seeri garinni loosu aana hosiisa

በማድረግ ተፈላጊውን ውጤት ላስመዘገቡ ስልጣኞች ተገቢውን የትምህርት ማስረጃቸውን በዲግሪ፣ በማስተርስና በዶክተሬት ዲግሪ የመስጠት፤

20)እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ የስልጠና፣ ጥናትና ምርምር ክፍሎችን ማቋቋምና ማጠናከር፤

21)ለትምህርት እና ህክምና አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ መርጃ መሣሪያዎችንና መፃሕፍትን ማሳተምና ማደራጀት፤

22)ከሀገር ውጭ ከሚገኙ መሰል ዩኒቨርሲቲዎችና የሕክምና ተቋማት ጋር ግንኙነት የመፍጠርና የሕክምና ቴክኖሎጂዎችንና መሣሪያዎችን በግዢም ሆነ በእርዳታ እንዲገኝ በማድረግ የህክምና ኮሌጁን አቅም የማሳደግ፤

23)ልዩ የትኩረት አቅጣጫ በሚፈልጉ የጤና ዘርፎች በቢሮው ወይም በመንግስት ሲፈለግ በልዩ ፕሮግራም የአጭርና የመካከለኛ ደረጃ ስልጠናዎችን በማዘጋጀትና በመተግበር የሰርተፊኬትና ዲፒሎማ ማስረጃ የመስጠት፣

24)የህክምና ኮሌጁ ሰራተኞችና ተማሪዎች ለሚያገኙት የህክምና አገልግሎት ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መፈፀም

25)ጤና ነክ የሆኑ ትምህርታዊ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስና በሕትመት ሚዲያዎች ወይንም በዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የማሰራጨት፣

26)የተማሪዎቸ ትምህርት ወጪ ክፍያ፣ የአገልግሎት ክፍያና ሌሎች ከተለያዩ ምንጮች የሚያገኛቸውን ገቢዎች በአግባቡ የመሰብሰብ በፋይናንስ ህግ መሰረት በሥራ ላይ የማዋል፡፡

27) Xagishshu kolleejje jawa qeecha fultino mannootira akkadamikete lophonna seertifikeetubba aa
28) Loosaasinetenna babbaxxitinno oggimmate baatooshshubba baata, tittirshu borde fushshitanno biddissinni gumulamanno.
29) Woloota hexxosi jeefisate dandiisiissanno fiixoontanno loossa loossanno.

## Gafa Sase

## Karsama, Qoossonna Gadachubba

**13.** Karsama

1) Qoqqowu mootimma Annimmanni galtanno Irgalamete Hospitaalenna Irgaalamete xaggishshu kolleejje mittu widira karsante haaru garinni Irgaalamete hospitaale xaggishshu kolleejje yaamamatenni tenne wodhonni karsantinno.
2) Konni quwi seeri heerirono uurrinshubba konni albaanni hospitaletennino iikko kolleeje widoonni assinanni hee'noonni assootubba loosoho hasiisanno garinni tantanante suffanno.

**14. Qoossonna Gadachote Sa'a**

1) Tenne wodho woloотu woro agarante heedhenna Irgaalamete hospitaalenna Irgaalamete xaggishshu kolleejje qoossonna gadachubba haaru garinni uurrittinno Yrgalamete hospitaale xaggishshu kolleejera sainno.
2) Konni quwi cinaanchu quwi (1) seeri saykki bissa qoossonna gadachono hanqafanno.

27) ለህክምና ኮሌጁ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች የአካዳሚክ ማዕረግና ሰርተፊኬቶችን የመስጠት፣
28) የሰራተኞችን እና የተለያዩ የሙያ አገልግሎት ክፍያዎችን መክፈል፡፡ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
29) ሌሎች ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ተዛማጅ ተግባራትን ያማከናዉናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መዋኸድ፣ መብትና ግዴታዎች

13. **መዋኸድ**

1) በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደሩት የይርጋዓለም ሆስፒታል እና የይርጋዓለም ህክምና ኮሌጅ ወደ አንድ ተዋህደው በአዲስ መልኩ ይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ በሚል በዚህ ደንብ ተዋህደዋል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ቢኖርም ተቋማቱ ከዚህ ቀደም በሆስፒታሉም ሆነ በኮሌጁ በኩል ሲከናወኑ የነበሩ ተግባራት ለሥራው በሚያመች መልኩ ተደራጅተው ይቀጥላሉ፡፡

14. **መብትና ግዴታ መተላለፍ**

1) የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የይርጋዓለም ሆስፒታል እና የይርጋዓለም ህክምና ኮሌጅ መብት እና ግዴታዎች በአዲስ መልኩ ወደ ተቋቋመው ይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ ተላልፈዋል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የሦስተኛ ወገኖችን መብትና ግዴታንም ይጨምራል፡፡

**GAFA SASE**

**Xagishshu Kolleejje Massagote Bissa**

**Biilloonye Loosonna**

**15. Xagishshu Kolleejje Massagote Bissa**

Kolleejjete aante noo massagote bissa heedhannose:

1) Borde
2) Manajimente
3) Senete
4) Qara Dayirektere
5) Layinki Qara Dayirektere
6) Akkadaamikete Komishiine.

**16. Bordennire**

1) Yirgaalamete hosipitaale xaggishshu kolleejje loosu massagaano borde (konni gedensaannni “Borde” yaamante woshshantannoti) tenne wodhonni urritino.
2) Bordete woshamanchima Biirote ikkitanno.

**17. Xagishshu Kolleejjeta Massagote Bordenna wo’ma Songo**

1) Boorde lamala huuro uytanno miilla nooseta ikkite miillate kiiro hasiisi garinni lexxitara dandiitanno.
2) Konni lallawi cinaancho quwa (1) hunda seerroonnihu heerirono xagishshu koleeje Qaru loosu jeefisiisaanchi bordete borreesaanchonna bordete gambooshirano beeqaancho ikke huuro aannokki manna ikkanno
3) Boordete gambisaanchi, layinki gambisaanchinna miilla garimma noonsa qoqqowu mootimma bissanna dagoomu kifillanni filante qoqqowu Faymate Biir shiqishonni qoqqowu Pirezedaantichi mooto’mitanno.
4) Boordete miilla owaantete diri onte diro ikkanno.

**ክፍል አራት**

**የህክምና ኮሌጁ አመራር አካላት**

**ሥልጣንና ተግባር**

**15. የህክምና ኮሌጁ አመራር አካላት**

ኮሌጅ የሚከተሉት የአመራር አካላት ይኖሩታል፡-

1) ቦርድ
2) ማኔጅመንት
3) ሰኔት
4) ዋና ዳይሬክተር
5) ም/ዋና ዳይሬክሮች
6) አካዳሚክ ኮሚሽን

**16. ስለቦርድ**

1) የህክምና ኮሌጁ የበላይ የስራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2) የቦርዱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል::

**17. የህክምና ኮሌጁ የአመራር ቦርድና ምልዓተ-ጉባኤ**

1) ቦርዱ ሰባት ድምጽ የሚሰጡ አባላት ያሉት ሆኖ የአባላቱ ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው ቢኖርም የህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ ፀሐፊና በቦርዱም ስብሰባዎች ተሳታፊ ሆኖ ድምጽ የማይሰጥ ሰው ይሆናል፡፡
3) የቦርዱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና አባላቱ አግባብነት ካላቸው የክልሉ መንግሥት አካላትና የኅብረተ-ሰብ ክፍሎች ተወጣጥተው በክልሉ ጤና ቢሮ አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማሉ፡፡
4) የቦርዱ አባላት የአገልግሎት ዘመን አምስት

Ikkirono hasiishshu garinni boordete miilla owaantete diri goofiro layinkimeeshsho mitte doyichora somantara dandiitanno.

5) Ayehuno boordete miili owaantete sufannokki gede assannohu ikkadu kori hee’rasi boordete widoonni xa’mo ka’inoha ikkiro Biirote qaagishshinni qoqqowu prezidantichi aye yannarano miiloomimmatenni kayisaranna wole worara dandaanno.

6) Xaggishshu kolleeje Layinki Qara Dayirektere boordete gambooshubba aana ayradu wosinchimmanni leellatenni dhaabbachishanno hedubba uytara dandiitanno. Ikkolana, kayinni boordete miilimmanni hanqafantaranna huuro uytara didandiitanno.

**18. Bordete Biilloonyenna Looso**

1) Xagishshu kolleejje Borde uurrinshate aliidi massagaano ikkite aaninno biilloonyi hee’rannose.

a/ Xagishshu kolleeje tenne wodho seeranna woloota garimma noonsa seerra loosu aana hosiisasenna uurrinshate giddo danchu gashshooti hee’rasi harunsanna buuxa;

b/ Xagishshu kolleejje mixo, baajeette, illachu raga, tantano, gashshootunna loosu amanyoote, giddo wodhonna akkaadamikkete pirogiraamubba lainohunni shiqqanosi hedubba buuxe kaajjishanna loosu aana hosansa harunsa; Xagishshu kolleejje qara dayirekterichinni shiqqanno hedo kaiminni laynki dayrekitorootanna woloota akkadaamikete sooreeyye hattono akkadaamikete komishiine miilla hasiisanno garinni doorantanno, somantanno woy gaamantanno amanyootenna owaantensa

ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም አስፈላጊነቱ ሲታመንበት ማንኛውም የቦርድ አባላት የአገልግሎት ጊዜያቸው ሲያበቃ ለዳግመኛ አንድ ጊዜ ሊሰየሙ ይችላሉ፡፡

5) ማንኛውም የቦርድ አባል በአገልግሎቱ እንዳይቀጥል የሚያደርግ በቂ ምክንያት ስለመኖሩ ከቦርዱ በኩል ጥያቄ የተነሣ እንደሆነ በቢሮው አሳሳቢነት ርዕሰ መስተዳድሩ በማናቸውም ጊዜ ከአባልነት ሊያነሳውና በሌላ ሊተካው ይችላል፡፡

6) የህክምና ኮሌጁ ም/ዋና ዳይሬክተሮች በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ በክብር እንግዳነት በመገኘት ገንቢ የሆኑ ሀሳቦችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን በቦርድ አባልነት ሊካተቱና ድምፅ ሊሰጡ አይችሉም፣

**18. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

1) የህክምና ኮሌጁ ቦርድ የተቋሙ የበላይ አመራር ሆኖ የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ/ የህክምና ኮሌጁ የዚህን ደንብና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጐች ሥራ ላይ ማዋሉንና በተቋሙ ውስጥ መልካም አስተዳደር መስፈኑን መከታተልና ማረጋገጥ፣

ለ/ የህክምና ኮሌጁን ዕቅድ፣ በጀት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ አደረጃጀት፣ የአስተዳደርና አሠራር ሥርዓት፣ የውስጥ ደንብና የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን በሚመለከት የሚቀርቡለት ሃሣቦችን መርምሮ ማጽደቅና ተግባራዊነታቸውን መከታተል፣

ሐ/ በህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር በሚቀርብ ሀሳብ መነሻነት ምክትል ዳይሬክተሮችና ሌሎች አካዳሚክ ኃላፊዎች እንዲሁም የአካዳሚክ ኮሚሽን አባላት እንደአግባቡ የሚታጩበት፣ የሚሰየሙበት ወይም የሚመደቡበት ሥርዓትና የአገልግሎት

yanna lainohunni biddissubba fushshanna garunni loosu aana hosansa harunsa;

d/ Garimma noo seerra jeefishshi noo gedeenni heedheenna ayeehuno layinkihu qaru dayrekterchi yawosi fulate widoonni jawa ikkitino laanfe leellishiro yawotenni hoolatenni sa'ne disippiliinete qaafo adha, dayrektericha la'annota ikkitanna biirote soorreessa amaalatenni qaafo adhanno gede assa;

e/ Xagishshu kolleejje ediiterootira baatooshshensa gumula;

f/ Xagishshu kolleejjeta istiraateejikete mixo, diru mixonna, baajeette shiqishanna kaajjitanno woyte jeefamansa haruunsa, uurrinshanniha loosu jeefishshu rippoortenna faynaansete xawishsha shiqishanna kaajjisha;

g/ Xagishshu kolleejjeta qara qaranna shiimammaadda eo garunni shallagote tajera amadamasenna fulo baajeettete garinni ikkansa harunsanna buuxa;

h/ Xagishshu kolleejje wolootu loosu massagaano bissa jawa bikka sa"ate looso loossano yannara woy jawa ikkinoha womaashshu hafanfarre huluullo hedhuro woy addanka xe'ne kalaqanturo umisi biilloony giddo hasiissanno qaafo adhanna hakkawoytenni biirote rippoorte shiqisha;

i/ Qoqqowu mootimmate loosaasinete lallawinna wodho wodhi-woro aana uurratenni gashshootunna tekinikete kaa'lo uytanno loosaasine qixire, deerru lopho, akata, dammozanna woloota addi-addi horo laino poolise hasiishshu garinni qixaabbanno gede assanna kaajisha;

ዘመናቸውን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣት እና በትክክል መተግበራቸውን መከታተል፡

መ/ አግባብነት ያላቸው ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኃላፊነቱን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ካሣዩ ከኃላፊነት ማሰናበትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ፣ ዳይሬክተሩን የሚመለከት ሲሆን የቢሮውን ኃላፊ በማማከር እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣

ሠ/ ለህክምና ኮሌጁ ኤዲተሮች ከፍያቸውን መወሰን፣

ረ/ የህክምና ኮሌጁን የስተራቴጂክ እቅድ፣ ዓመታዊ እቅድና በጀት ማቅረብና ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፣ የተቋሙን የክንውን ሪፖርትና የፋይንስ መግለጫን ማቅረብና ማፅደቅ፤

ሰ/ የህክምና ኮሌጁ ዋና ዋና እና ጥቃቅን ገቢዎቹን ትክክለኛ የሂሣብ መዝገብ መያዙንና ወጪዎች በበጀት መሠረት መሆናችውን መከታተልና ማረጋገጥ፣

ሸ/ የህክምና ኮሌጁ ሌሎች የአመራር አካላት ከባድ የመጣስ ተግባር በሚፈጽሙበት ጊዜ ወይም ከባድ የሆነ የገንዘብ ብክነት ስለመከሰቱ ጥርጣሬ ካለ ወይም በእርግጥ ተከስቶ ከሆነ በራሱ ስልጣን ውስጥ ተገቢውን የመፍትሄ እርምጃ መውሰድና ወዲያውኑ ለቢሮ ሪፖርት ማቅረብ፤

ቀ/ በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅና ደንቦች መሠረታዊ መርሆች ላይ በመመስረት ያስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ቅጥር፣ እድገት፣ ዲሲፒሊን፣ ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ-ጥቅሞችን የሚመለከት ፖሊሲን እንደአስፈላጊነቱ እንዲዘጋጅ ማድረግና ማጽደቅ፤

j/ Xagishshu kolleejje la’ano hajubba aana taje xa’ma, afi’ranna biirote woy ministerete rippoorte assa;

k/ Kolleejjete muro aana koffeenyu shiqiro buuxanna jeefote gumulo aa;

l/ Kunni quwi cinaanchu quwi aantete fidale /k/ woro noo gedeenni heedhenna xagishshu kolleejje koffeenya rankete doogonni haadhe tirtanno gari uurrinshate ammanyoote agadhinnoha ikkasi buuxa hasisanno;

m/ Xagishshu kolleejje akkadaamikete kifilla, gashshootu bissa, loosu jeefishshi diinichchu rippoorte kaiminni mixote garinni keena;

n/ Akkadaamikete komishiine gumulonna fushitannoha akkadaamikete seerra gumulamasi harunsa;

o/ Baalanta xagishshu kolleejje diinenna woy akkadaamikete komishiinenni sa’ino muro uurrinshannita ajuuja miiccannota woy tenne wodho woy woloota gobboomu seerra gurchidhannota ikkite leelturo muro woy gumulo kaysa;

p/ Umisi loosu amuraatenna giddo gashshooti wodhonna miilla la’annota disippiliinete wodho fushsha;

q/ Pirofeeserimmate deerru suusi lopho akkadaamikete komishiinenni shiqquro kaajjishsha;

r/ Dayrekterchunni shiqqanno amaale aana safamatenni xagishshu kolleejje rosoho baatisiisannoha addi-addi baatooshshi dananna jilba mura hattono qoqqowu gashshooti amaale mini gumullinno kaiminni uurrinshannita eo hedote giddo woratenni addi-addita baatantanno barru hoshsho, tirfete yanna baatooshshenna labbinore gumulsiisa;

s/ Senetete lejisleeshine buuxe kaajjisha.

2) Xagishshu kolleejje Borde miilla afidhanno horo biirotenni gumullanniha ikkanna baajeno uurrinshate gaamannita ikkite uurrinshate

በ/ የህክምና ኮሌጁን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መረጃ የመጠየቅና የማግኘት እና ለቢሮው ወይም ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማድረግ፣

ተ/ በኮሌጀ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ሲቀረብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት፤

ቸ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ተ/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የህክምና ኮሌጁ ቅሬታዎችን በተፋጠነ መንገድ ተቀብሎ የሚፈታበት የተሟላ ተቋማዊ ስርዓት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣

ነ/ የህክምና ኮሌጁን አካዳሚክ ክፍሎች፣ የአስተዳደር አካላቱን የስራ አፈፃፀም በዲኑ ሪፖርት መሠረት ከእቅድ አኳያ መገምገም፤

ኀ/ የአካዳሚክ ኮሚሽን ውሳኔዎችና የሚያወጣቸው የአካዳሚክ ህጎች መፈፀማቸውን መከታተል፤

አ/ በየህክምና ኮሌጁ ዲን ወይም አካዳሚክ ኮሚሽኑ የተላለፈ ውሳኔዎች የተቋሙን ተልዕኮ የሚጎዱ ወይም ይህንን ደንብ ወይም ሌሎች የሀገሪቱ ህጎች የሚቃረኑ ሆነው ሲገኙ ውሳኔወቹን መሻር፣

ከ/ የራሱን የአሰራር ስነ-ስርአትና የውስጥ አስተዳደር ደንብና አባላቱን የሚመለከት የዲሲፒሊን ደንብን ማውጣት፣

ኸ/ የፕሮፌሰርነት የማዕረግ እድገትን በአካዳሚክ ኮምሽን ሲቀርብለት ማጽደቅ፣

ወ/ በዳይሬክተሩ በሚቀርብ ምክር ላይ ተመስርቶ የህክምና ኮሌጁ ለትምህርት የሚያስከፍላቸውን የተለያዩ ክፍያዎች ዓይነትና መጠን መወሰን እንዲሁም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በወሰነው መሠረት የተቋሙን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ተከፋይ አበሎችን፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎችንና የመሳሰሉትን መወሰን፣

ዐ/ የሴኔት ሌጅስሌሽኑን መርምሮ ማፅደቅ

2) የህክምና ኮሌጁ ቦርድ አባላት ጥቅማ-ጥቅሞች በቢሮ የሚወሰን ሲሆን በጀቱም ከተቋሙ

dhuka hedote worinoha ikka noosi.

**19. Bordenniha Uurrinshu Gambooshshe**

1) Bordennihu xaaddote gambooshshi dirunni sasunni kayse shoolu geeshsha ikkara dandaanno.
2) Rosamino gambooshshi yannara Borde qeechase fulate dandiisiisanose garinni baxxinohunni mixotenna baajeettete qixxaawo hattono jeefote aana irko assate injiitanno yannara ikkanno gede assitanno.
3) Kunni quwi cinaancho quwi (2) agarantinno gede heedhenna Bordete massagaanchi woshshattonni woy huuro aate qosso noonsa miilanni mittu sayikkihuni (1/3) xa'mitanno yannara wiinamunni gambooshshe assa dandiitanno.
4) Bordete gambisaanchi baalanti Bordete gambooshshubba ikkado qixaawo assinoonninsata ikkase, sanadda qorophishshunni agarantinottanna, amadantinnota, borde hajajanno garinni gumulo garunni la'annonsarira sa'inotta buuxa noosi.

**20. Bordete Miiloomimma Uurra**

Bordete miiloomimma aantinno korkaatubbanni uurritara dandiitanno.

1) Biiro fushshitanno biddissi garinni loosu yanna gooffuro.
2) Fajjosinni miiloomitetenni aguratenni.
3) Rewootenni, dhibbuni woy jawa jaddote hunaancho ikke leellatenni.
4) Jawa hunaanchimmanni, dandoo hoogatenni woy gambooshshu aana leellate jawa ikkitinota laanfe leellishatenni woy gandaa

የሚመደብ ሆኖ የተቋሙን አቅም ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

**19. ስለቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች**

1) የቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች በዓመት ከሦስት እስከ አራት ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡
2) የመደበኛ የስብሰባው ጊዜ ቦርድ ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው መልኩ በተለይም የእቅድና የበጀት ዝግጅቶች እንዲሁም አፈፃፀም ላይ አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችል በሚያደርገው ወቅቶች እንዲሆን ያደርጋል፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርድ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አባላት አንድ ሦስተኛው (1/3) በሚጠይቁበት ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ማድረግ ይችላል፡፡
4) የቦርዱ ሰብሳቢ ሁሉም የቦርዱ ስብሰባዎች በቂ ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን፣ ሰነዶች በጥንቃቄ መጠበቃቸውንና መያዛቸውን፣ ቦርድ በሚያዘው መሠረት ውሣኔዎቹ በትክክል ለሚመለከታቸው መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**20. የቦርድ አባልነት መቋረጥ**

የቦርድ አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡፡

1) ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ፤
2) በፈቃደኝነት ከአባልነት በመልቀቅ፤
3) በሞት፣ በሕመም ወይም በከባድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘት፣
4) በከባድ ጥፋት፣ ችሎታ ማጣት ወይም ሰብሳቢዎች ላይ ለመገኘት ከባድ የሆነ

hoogatenni.

5) Biiro borde wo'munni wo'ma soorrate woy badde soorrate gumulote aana iillituro.

## 21. Bordete Loosu jeefishshi Keenore

1) Borde woyyaabinno massago aate dandiisiisannose huwanyo afi'rate umiseha loosu jeefishshi keeno assa noose.
2) Borde loosu jeefishsha keenate huuro aate qoosso noonsa miillanninna xagishshu kolleejje qara dayrekitere noowa cufo gambooshshe ha'rissanno.
3) Bordete massagaanchi keenoonni guma yanna yannatenni gashshootu amaale miniranna biirote rippoorte assanno. Bordete massagaanchi biirote ledo xaaddotenni gutu bare dirunni lame hige qixxeesanno.
4) Borde keeno mamootenna hiitto ha'risannoro gumultanno, ikkirono dirunni ajani ajeenna mitto ha'runsote keenonna mitto xaphoomu keeno assa noose.

## 22. Managimentete Biilloonyenna looso

1) Qara qara istiratejikete hajubba aana qara dayrekitericha amaaltanno;
2) Xagishshu kolleeje xaphooma loosu millimillo aana hasaabbanno gumulote raga worttanno;
3) Mixote, baajeetette horoonsishsha, tantano, rosu pirogiraamubba biddissa, rosu kifilla karsamanna babbaxa kaimu hedonna jeefishshu ripoorte aana hasaabbanno;
4) Odiitete ripoorte lainnohunni tirranni doogo hasaabbe gumulote bordete shiqisha;
5) Rosiisaano ikkitinnokki xagishshu kolleeje ogeeyyera deeru lopho uysiissanno woy hooltanno umise safaraano fushsha;

ድክመት በማሳየት ወይም ባለመቻል

5) ቢሮው ቦርዱን ሙሉ ለሙሉ ለመቀየር ወይም በከፊል ለመለወጥ ውሣኔ ላይ ሲደርስ፡፡

## 21. ስለቦርድ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ

1) ቦርዱ የተሻለ አመራር ለመስጠት የሚያስችለውን ግንዛቤ ለማግኘት የራሱን የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
2) የቦርዱ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ድምጽ የመስጠት መብት ባላቸው አባላትና የህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር በተገኙበት በዝግ ስብሰባ ያካሄዳል፡፡
3) የቦርዱ ሰብሣቢ የግምገማውን ውጤቶች በየወቅቱ ለመስተዳደር ምክር ቤትና ለቢሮው ሪፖርት ያደርጋል፡፡ የቦርድ ሰብሣቢው ከቢሮው ጋር መደበኛ የጋራ መድረክ በዓመት ሁለት ጊዜ ያዘጋጃል፡፡
4) ቦርዱ ግምገማውን መቼና እንዴት እንደሚያካሄድ ይወስናል፤ ሆኖም በዓመት ቢያንስ አንድ የክትትል ግምገማ አንድ የማጠቃለያ ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 22. የማኔጅመንት ሥልጣንና ተግባር

1) በዋና ዋና ስተራቴጅክ ጉዳዮች ላይ ዋና ዳይሬክተር ያማክራሉ፣
2) በህክምና ኮሌጁ አጠቃላይ የሥራ ዕንቅስቃሴ ላይ ይወያያሉ፤ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፣
3) የዕቅድ ፤በጀት አጠቃቀም፤ አደረጃጀት፤ የትምህርት ፕሮግራሞች መመሪያ፤ የትምህርት ክፍሎች መደበላለቅና መለያየት ረቅቅ ሀሳብና የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ ይወያያሉ፣
4) ኦዲት ርፖርትን በተመለከተ የመፍትሄ አቅጣጫ ተወያይቶ ለዉሳኔ ለቦርዱ ማቅረብ፣
5) መምህራን ላልሆኑ ለህክምና ኮሌጁ ባለሙያዎች ደረጃ ዕድገትን የሚያሰጡ

6) Xagishshu owaante aate gara, hala’llanna lophora qara qara hajjubba badatenni loosu aana hosiisate loossanno hasaawano assitanno;
7) Qoqqowunna gobbate deerinni fultanno seerra garunni loosamansa buuxanno. Konnira ledotenninno xagishshu kolleejera uynanni xagishshu owaante gobbate hattono qoqqowu seerra garinni loosamansa buuxxanno;
8) xagishshu kolleeje isitiratejikete mixo qixaawo assannna qixxaawono bordete shiqasira albaanni hasaawanna kaajjisha;
9) Managimentete gambooshe aganunni ajiha ajeenna lame hige assittanno, gambooshu wo’ma songo 2/3 miilla leeltinnowa ikkanno ikkollanna kaynni huuro uytanno rooridi miilla leelturo gambooshe harisa dandiitanno;
10) Gambooshu songi-qaali borreesaancho gambisaanchu miillate mereerrinni doore riqiwinno mancho ikkanno;
11) Gambooshu yannara yekkersiissanno hedubba kauro huurote roorrenni gumullanni. Ikkeenano taalo huuro borresanturonna gumulate mitiinsituro ikkitanno woyte gambisaanchu irkisino hedo jeefantannoha ikkanno;
12) Qaru dayrekiterichinni woy dayrekiterichu riqiwamaanchi gobbaanni yekkeersiissanno manajimentete gumullo woy hajubbanna gumansa saykki bisi ledo xaadooshshe assano ikko mashshallaqqe aa dinose.

**23. <u>Xagishshu Kolleejje Seneete Uurrisa</u>**

Xagishshu kolleejje seenete xagishshu kolleejje qara dayirekterenni uurritannoha ikke tittirsha baalante xagishshu kolleejje seneete lejisileeshiine

ወይም የሚከለክሉ የራሱን መስፈርቶች ማዉጣት፣

6) ለህክምና አገልግሎት አሰጣጥ፣ መስፋፋትና ማደግ ዋና ዋና ጉዮችን በመለየት ለተግባራዊነቱ ይሰራል ውይይትም ያደርጋል፣
7) በክልልና ሀገር ደረጃ የሚወጡ ህጎች በአገባቡ መተግበራቸዉን ያረጋግጣል:: ከዚህ በተጨማርም በኮሌጁ የሚሰጠዉ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ በሀገርቷ ብሎም በክልሉ ህጎች መሠረት መተግበራቸዉን ያረጋግጣል፣
8) የህክምና ኮሌጁን ስትራቴጅክ ዕቅድ ዝግጅት ማድረግ እና ዝግጅቱንም ቦርድ ከመቅረቡ በፊት መወያየትና ማጽደቅ፣
9) ማኔጅመንቱ በየወሩ ቢያሰንስ ሁለት ጊዜ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ የስብሰባዉ ምላተ-ጉባዔ 2/3 አባላቱ በተገኙበት ይሆናል፤ ሆኖም ግን አብላጫ አባላት ከተገኙ ስብሰባዉን ማካሄድ ይችላል፣
10) የስብሰባዉ ቃሌ-ጉባኤ ፀሐፊ ሰብሳቢዉ ከአባላቱ መርጦ የወከለዉ ሰዉ ይሆናል፣
11) በስብሰባዉ ወቀት አከራካሪ ሀሳቦች ከተነሱ በአባለጫ ድምጽ ይወሰናል፡፡ ሆኖም ግን እኩል ድምጽ ከተመዘገበ እና ለዉሳኔ አስቸጋር በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢዉ የደገፈዉ ሀሳብ ተፈጻሚ ይሆናል፣
12) ከዋና ዳይረክተሩ ወይም ከዳይረክተሩ ተወካይ ዉጭ አከራካሪ የሆኑ የማኔጅሜንቱን ዉሳኔ ወይም ጉዳዮችን እና ዉጤታቸዉን ከሶስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት ማድረግም ሆነ መረጃ መሰጠት የለበትም፡፡

## 23. <u>የህክምና ኮሌጁ ሴኔት መቋቋም</u>

የህክምና ኮሌጁ ሴኔት በህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር የሚቋቋም ሆኖ ዝርዝሩ በህክምና ኮሌጁ ሰኔት ሌጅስሌሽን በተመለከተው

wortino garinni ikkanno.

24. **Xagishshu Kolleejje Seneetete Miilla**

1) Xagishshu kolleejje qaru dayrekterchi ---------------------------------------------------gambisaancho
2) Layinki qaru dayrekterchi -------------------miila
3) Registeraarete aluminay dayrekterchi---….miila
4) Lamu akkadaamikete loosaasine--------miilla
5) Mittu rosaanote riqiwamaanchi ---------miila
6) Xaggishshu owaante rosi islaanchimma woyyaanbenna inoveshine dayrekitore ………………………………………..miilla
7) Maxxaffate mini gaamo massagaanchi…miilla

25. **Xagishshu Kolleejje Seneete Biilloonyenna Loossa**

Seenete aante noo biilloonyenna loossa heedhannose:

1) Xagishshu kolleejje rosu pirogiraamenna amuraate loosu aana hossanno gede assitanno.
2) Borde fushshitanno biddissi aana kaima assatenni rosaano massagate ikkito, xagishshu kolleejje rosu hajubba, rosu golla sooreeyye doorama, qixirete deerranna addi addi horo akatunna akkadaamikete loosaasine baatooshshe lainohunni giddoydi biddissi fulanno.
3) Akkadaamiketenna xagishshu loosaasine qixire kaajjishshanno, pirofeeserinnetete suusa uynanni gede Bordete hedo shiqishshanno.
4) Rosaano adha, rosu deerri gumulsha, disippiliinete hajubbanna maasso la'ino keenote safaraano fushshitanno, tenne hajubba aana ka''anno koffeenyi buuxe gumula
5) Fonqolunna deerra aate gara xaphooma gara gumulanno.
6) Seennu rosaano adhanna/rosiisa assinanni

መሰረት ይሆናል፡፡

24. **የህክምና ኮሌጁ ሴኔት አባላት**

1) ህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይሬክር----------ሰብሳቢ
2) ምክትል ዋና ዳይረክተሮች---------------አባል
3) የሬጅስትራር አሉሚናይ ዳይሬክተር----አባል
4) ሁለት የአካዳሚክ ሠራተኞች ----------አባል
5) አንድ የተማሪዎች ተወካይ--------------አባል
6) የህክምና አገልግሎት ትምህርት ጥራት ማሻሻያና ኢኖቬሽን ዳይሬክተር……. አባል
7) የቤተ-መጽሀፍት ቡድን መሪ ………አባል

25. **የህክምና ኮሌጁ ሴኔት ስልጣንና ተግባር**

ሰኔቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የህክምና ኮሌጁ የትምህርት ፕሮግራምና ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
2) ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ላይ በመመስረት የተማሪዎች አስተዳደር ሁኔታ፤የህክምና የኮሌጁን የትምህርት ጉዳዮች፤ የትምህር ክፍሎች ኃላፊዎች አመራረጥ፤ ቅጥር ደረጃና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን ስነ-ምግባርና የአካዳሚክ ሠራተኞች ደመወዝ በተመለከተ የውስጥ መመሪያ ያወጣል፤
3) የአካዳሚክና የህክና ሠራተኞችን ቅጥር ያፀድቃል፤ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለቦርድ ሀሣብ ያቀርባል፤
4) የተማሪዎች ቅበላ፤ የትምህርት ደረጃ አወሳሰን፣ የዲሲፕሊን ጉዳዮችንና ምርቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ያወጣል፤ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚነሱትን ቅሬታዎች መርምሮ ይወስናል፡፡
5) የፈተና እና የደረጃ አሰጣጥ አጠቃላይ አቅጣጫ ይወስናል፡፡

kaa'lo amuraate diriirsanno.

7) Maassote yanna pirogiraamma aana rosaanote adha amuraate diriirsanno. Maassono kaajjishshanno.
8) Umisiha gambooshshunna loosu amuraate fushshanno.
9) Hasiisiha ikkiro umisi biilloonyenna assootta xagishshu kolleejje bissara uurrinshatenninna yannate geeshsha uurrinsanni komitera sayissara dandiitanno.
10) Bordetenni aamantanno wole loossanno qineessitanno.

**Gafa Shoole**

**Xagishshu Kolleejje Qara Dayirekiterenna 2ki Dayirekteroota Mootoo'ma, Biilloonyenna Loosu Qeechannna Owaantete Uurra**

**26. Xagishshu Kolleejje Qara Dayirekterenna 2ki Dayrekterooti Mootoo'manna Loosu Jeefishshi Keeno**

1) Qaru dayrekiterichi 80% heewotenni 20% anga Biirote shiqeenna wonshitannoha ikkanno.
2) Aantaanchu dayrekiteroota 80% heewotenni 20% anga Bordete shiqeenna wonshitannoha ikkanno.
3) Konni quwi cinaancho quwa (1) nna (2) seerroonnihu heerirono xagishshsu kolleeje filamaano dayrekitoreetotinna aantaano dayrekitoreetoti akadamikete massaggonna gashshooti dandoo noonsa hattono urrinshate soorronna lophora qixxaabbinnonna bayriidi seeriranna mootimmate poolisubba adhitinnore ikka noonsa.
4) Heewotenna doorshu amanyooti tittirote biddissa Biiro fushshitanno.
5) Xagishshu kolleejje qaru dayrekterchi loosu yanna

6) የሴት ተማሪዎች ቅበላና የሚደረጉ ድጋፎች ሥርዓት ይዘረጋል፤
7) የድህረ ምርቃ ፕሮግራሞች ላይ የተማሪዎች ቅበላ ሥርዓት ይዘረጋል። ምርቃዉንም ያፀድቃል፤
8) የራሱን የስብሰባ እና የአሰራር ሥርዓት ያወጣል፤
9) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ የራሱን ስልጣንና ተግባራት ለህክምና ኮሌጁ አካላት በቋሚነትና በጊዜያዊነት ለሚቋቋሙት ኮሚቴዎች ሊያስተላልፍ ይችላል፤
10) በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል።

**ክፍል አምስት**

**ስለ ህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይረክቴር እና ምክትል ዋና ዳይረክተሮች ሹመት፣ ሥልጣንና ተግባር እና የአገልግሎት መቋረጥ**

**26. ስለ ህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይሬክርና ምክትል ዋና ዳይረክተሮች ሹመትና የስራ አፈፃፀም ግምገማ**

1) ዋና ዳይሬክተሩ 80% በውውድድር ሆኖ 20% ለቢሮው ቀርቦ ይሞላል።
2) የምክትል ዳይሬክተሮች 80% በውውድድር ሆኖ 20% ለቦረዱ ቀርቦ ይሞላል።
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም የህክምና ኮሌጁ እጩ ዳይሬክተሮች እና ምክትል ዳይሬክተሮች የአካዳሚክ መሪነት እና የአስተዳደር ክህሎት ያላቸው እንዲሁም ለተቋማዊ ለውጥና እድገት ዝግጁ የሆኑና ህገ መንግስቱን እና የመንግስት ፖሊሲዎች የተቀበሉ መሆን ይኖርባቸዋል።
4) የውድድርና የምርጫ ስነ-ስርዓት ዝርዝር መመሪያ በቢሮው ይወጣል።
5) የህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይረክቴር የስራ ዘመን

lee diro ikkanna, 2[ki] qara dayrekiterootihu shoole diro ikkanno. Ikkironno wirro wirro mootoo’ma dandiitanno.

6) Borde, qara dayirekterenna 2ki dayrektere jeefishshi harunsonna keeno dirunni lame higge ha’rissanno.

7) Xaaddonnihu qaru dayrekterchinna 2ki qara dayrektere somama hoogguro agadhaancho dayrektere woy agadhaano qara 2[ki] dayrektere ikke 180 geeshsha keeshsha dandaanno. Ikkirono xawinsoonni yanna giddo tenne wodhonna lallawunni seerroonni garinni biirote baxxitinno gumullo aa hoongiro noowa sufanno.

**27. <u>Xagishshu Kolleejje Qaru Dayrekterichi Biilloonyenna Loososi</u>**

Bordete yawo noo gedeenni heedheenna qaru dayrekterchi xagishshu kolleejje qara loosu jefisiisancho ikke konni woroonni no biilloonyinna loosu qeechi heedhannosi:

1) Xagishshu kolleejjete owatamaanote aana illacha tuggino xagishshu owaante wo’mu garinni uyitanni noota buuxanno;

2) Kolleejjete hexxonna ajuuja wonshate massaganno, gashshanno;

3) Xagishshu kolleejje bissanna dagoomu aliidi rosu hexxonna xagishshu kolleejje massago kasso ayirrisansa buuxxanno;

4) Xagishshu kolleejje qoqqowu fayyimmate handaarira hasi’nanni bikkanna dani luphiima silanchimma harunse ikkadimma noonsa fayyimmate maassamaano burqisasi buuxxanno;

5) Rosa, rosiisanna xiinxallo jawaachishshannota dancha kolleejjete dagooma kalaqanno,

ስድስት ዓመት ሲሆን የምክትለ ዋና ደይረክቴሮች አራት ዓመት ይሆናል። ሆኖም በተደጋጋሚ ሊሾሙ ይችላሉ።

6) ቦርዱ የዋና ዳይሬክተሩንና ምክትል ዳይሬክተሩን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በዓመት ሁለት ጊዜ ያደርጋሉ

7) መደበኛ ዋና ዳይረክቴርና ምክትል ዋና ዳይረክቴሮች ካልተሰየሙ ተጠባባቂ ዳይሬክቴር ወይም ተጠባባቂ ምክትል ዋና ዳይረክቴር ሆኖ እስከ 180 ቀናተ መቆየት ይችላሉ። ሆኖም በተጠቀሰዉ ጊዜ ዉስጥ በዚህ ደንብ እና በአዋጁ በተደነገገው አግባብ በቢሮው ልዩ ዉሳኔ ካልተሰጠ ቋሚ እንደሆነ ይቆጠራል፡

**27. <u>የህክምና ኮሌጁ ዋና ዳይረክቴር ስልጣንና ተግባር</u>**

የቦርዱ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይረክቴሩ የህክምና ኮሌጁ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1) ህክምና ኮሌጁ ተገልጋይ ተኮር የህክምና አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ እየሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፤

2) የህክምና ኮሌጁን ዓላማና ተልዕኮ ለማሣካት ይችል ዘንድ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

3) የህክምና ኮሌጁ አካላትና ማህበረሰብ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የህክምና ኮሌጁን መሪ እሴቶች ማክበራቸውን ያረጋግጣል፤

4) የህክምና ኮሌጁ ክልሉ በጤናው ዘርፍ በሚፈልገው መጠንና ዓይነት ከፍተኛ ጥራትን የተከተለ ብቃት ያላቸውን የጤና ምሩቃንን ማፍራቱን ያረጋግጣል፤

5) መማር፣ ማስተማርንና ምርምርን የሚያበረታታ ምቹ ተቋማዊ ሁኔታን

harurnse uurrisanno;

6) Xiinxallotenna amaalate looso baalantera balaxo uuyinanni goboomunna qoqqowu deerri hajo aana assinoonita buuxanno;

7) Hexose wonshate hajo la'anonsa federaaletenna qoqqowu bissa, garimma noonsa mootimmanna mootimmatte gobbaanni ikkitinno uurinshubba ledo sufanchu xaadooshshi kalaqamanno gede assanno;

8) Mannu wolqanni, tantanotenninna loosu harinshonni uurrinshate ikkado ajuuja quwamino xuku noohu giddo massagaanonna gashshooti amanyooti hee'ranno gede assanno;

9) Akkadaamiketenna xagishshu owaante sooreeyyenna akkaadaamikete komishiine miilla sommanni amanyoote qixeessatenninna Bordetenni kaajishatenni loosu aana hosiisanno;

10) Rosunninna xiinxallote garimma, silanchimma uurrinshate wolaphonna xa'mamooshshi, owaante aate guminninna fulo ajishate wodho aana uurrine rosu golla tantano seenetetenna Bordete shiqishe gumulsiisanno, fajjiniro loosu aana hosiisanno;

11) Qixirete sooreessimmate baychubba looso gaammanniti yawote battala heewotenni amandanita ikkasenna yawotenni ka''ano loosu jeefishshi keeno, disippiliinete hajonna owaantete diri goofa aana calla safamase buuxxanno;

12) Uurrinshate deerrinni bikkaasine qixxeessanno, urrinshunniha akkadamiketenna gashshootu

ይፈጥራል፣ በቀጣይነት ይገነባል፤

6) የምርምርና የማማከር ተግባር ሁሉ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሀገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች ላይ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

7) ዓላማውን ለማሳካት ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት፣ አግባብነት ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በዘላቂነት ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል፤

8) በሰው ኃይሉ፣ በአደረጃጀቱና አሰራሩ ለተቋሙ ተልዕኮ የሚመጥን ብቃት ያለው የውስጥ አመራርና አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖረው ያደርጋል፤

9) የአካዳሚክ እና የህክምና አገልግሎት ኃላፊዎችንና የአካዳሚክ ኮሚሽን አባላትን የአስያየም ሥርዓትን በማዘጋጀትና በቦርዱ በማፅደቅ በተግባር ላይ ያውላል፤

10) በትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ በተቋማዊ ነፃነትና ተጠያቂነት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትና በወጪ ቆጣቢነት መርሆች ላይ በመመስረት የትምህርት ክፍሎች አደረጃጀትን ለሴኔቱና ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤ሲፈቀድም በተግባር ላይ ያውላል፤

11) የቅጥር ኃላፊነት ቦታዎች በውድድር የሚያዙ መሆኑንና ከኃላፊነት መነሳትም በሥራ አፈፃፀም ግምገማ፣ በዲሲፕሊን ጉዳይ እና በአገልግሎት ዘመን ማብቃት ብቻ ላይ ተመስርቶ መሆኑን ያረጋግጣል፣

12) ተቋማዊ የደረጃ መለኪያዎችን ያዘጋጃል፤ የተቋሙ የአካዳሚክ እና የአስተዳደር ስራዎች በወጡት መለኪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣

loossa fultino bikkaasine garinni jeefamase buuxxanno;

13) Eonna fulo garimma noonsa faynaansete seeri kaiminni milli yaasenna amadamase buuxxanno;

14) Senetetenna woloотu gashshootamenna godooydi gambooshuwa ikkadu qixxaawoninna yannase agartino garinni harinsoonnita, ikkadu garinni mareekantinotanna gambooshshu ajanddi agaraminota hatono hajote aana assinanni hasaawi baalanta kamaalinoha ikkasinna senetete gumulo hajo la'anonsa bissara garunni sayinsoonnitanna loosu aana hosase buuxanno;

15) Baalante xagishshu kolleejje giddo woy baalante xagishshu kolleejje sayikki baadi mereero ka'annota sumuu yaa hoogate qarra uurrinshate ajuujanna horo wonshate widoonni keerunninna seerunni tirantanno gede assanno;

16) Xagishshu kolleejje millimillonna safote namoomme baalanti hasiisanno tajete maareekko amanyootinni mareekamase, taje garunni agaramasenna bordete, urrinshshu dagoomira, mootimmatenna garimma noonsa wolootu bissara iillinoha ikkasi buuxanno;

17) Xagishshu kolleejje giddo no lubbonna jajja agarate dandiisiisanno woowe noosi dano gargaranninna agarooshshu amurati ijaaramanno gede assanno;

18) Xagishshu kolleejjeha seedanna harancho yanna mixonna baajeette qixeessanno, kaajjiturono jeefisanno;

19) Xagishshu kolleejje mixo jeefishsha Bordetenna hajo la'anosi golira yanna agadhitinno

13) ገቢና ወጪ አግባብነት ባላቸው የፋይናንስ ሕጎች መሠረት መንቀሳቀሳቸውንና መያዛቸውን ያረጋግጣል፣

14) የሴኔት እና ሌሎች አስተዳደራዊና ውስጣዊ ሰብሰባዎች በበቂ ዝግጅትና ወቅታቸውን ጠብቀው መካሄዳቸዉን፣ በበቂ ሁኔታ መመዝገባቸውን እና ቃለ ጉባኤዎቹ መጠበቃቸውን በጉዳዮች ላይ የሚደረገው ውይይት ሁሉንም የዳሰሰ መሆኑን እና የሴኔት ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው በትክክል መተላለፋቸውን እና መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

15) በህክምና ኮሌጁ ውስጥ ወይም በህክምና ኮሌጁና በሦስተኛ ወገኖች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን የተቋሙን ተልዕኮና ጥቅሞች ከማሳካት አኳያ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፤

16) የህክምና ኮሌጁ እንቅስቃሴና መሠረታዊ ግንኙነቶች በተገቢው የመረጃ ሥርዓት መመዝገባቸውን፣ መረጃው በአግባቡ መጠበቁን እና ለቦርዱ፣ ለተቋሙ ማህበረሰብ፣ ለመንግስት እና አግባብነት ላላቸውም ሌሎች አካላት ተደራሽ መሆኑን ያረጋግጣል፣

17) በህክምና ኮሌጁ ውስጥ ያለ ህይወት እና ንብረትን ለመጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ የአደጋ መከላከያ እና የጥበቃ ስርዓት እንዲገነባ ያደርጋል።

18) የህክምና ኮሌጁን የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ያስፈጽማል፤

19) ስለ ህክምና ኮሌጁ እቅድ አፈፃፀም ለቦርዱና ለሚመለከተው ክፍል ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት እና መረጃ ያቀርባል፤

20) የህክምና ኮሌጁ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ማናቸውም ግንኙነት

rippoortenna mashalaqe shiqishshanno;

20) Xagishshu kolleejje sayikki baadi ledo assitannoti ayee dani xaadooshshino uurrinsha riqiwanno;
21) Xagishshu kolleejjete su’minni fayinaansete amuraate harunse baankete shallago fananno, milli assanno;
22) Gobbate gobaayidi fulo balanxxe mixi’noonninna urrinshshaho noonsa horo aana calla xintantinota ikkase buuxanno;
23) Ikkitote gadachamanni loosu aana leellannokki yannara layinki qara dayrekterootinni mitto riqiwa dandaanno;
24) Wo’ma yannasi urrinshshate loossa aana hosiisanno, owaanteteno garimma noosi aganu baatooshshenna addi addi horo afi’ranno;
25) Bordete bande uyinaanisi woloota loossa loosanno.

**28. <u>Layinki Qara Dayirekiteroota</u>**

Xaggishshu kolleeje massagantannohu qaru dayrekiterichinni ikke aante noo aantaano dayrekiterooti heedhannosi;-

1) mittu xiinxallo, rosunna qajeelshu layinki qara dayrektere,
2) mittu gashshootunna latishshu layinki qaru dayrekterchi, qoleno
3) Mittu xagishshu owaante layinki dayrekterchi hee’ranno.

**29. <u>Xinxallote, Rosunna Qajeelshu Layinki Qaru Dayrektere Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

1) Xagishshu kolleejje xaphooma akkaadaamiketenna xinxallote loossa lainohunni gumulote hedo qixxeesse qaru dayrekterchira shiqishanno;
2) Xagishshu kolleejje akkadaamikete kalaandere

ተቋሙን ይወክላል፤

21) በህክምና ኮሌጁ ስም የፋይናንስ ሥርዓትን ተከትሎ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤
22) የውጪ ጉዞዎችን ቀድመው የታቀዱና ለተቋሙ በላቸው ፋይዳ ላይ ብቻ የተመሠረቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
23) በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሥራው ላይ በማይገኝበት ጊዜ ከምክትል ዋና ዳይረክቴሮች አንዱን ሊወክል ይችላል፡፡
24) ሙሉ ጊዜውን በተቋሙ ስራዎች ላይ ያውላል፤ ለአገልግሎቱ ተገቢውን ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅሞች ያገኛል፣
25) በቦርዱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**28. <u>ስለ ምክትል ዋና ዳይረክተሮች</u>**

የህክምና ኮሌጁ የሚመራው በዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት ምክትላን ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፤-

1) አንድ የምርምር፣ትምህርትና ስልጠና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣
2) አንድ አስተዳደር እና ልማት ም/ዋና ዳይሬክተር፣ እንዲሁም
3) አንድ ህክምና አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ይኖረዋል፡፡

**29. <u>የምርምር፣ ትምህርትና ስልጠና ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስልጣንና ተግባር</u>**

1) የህክምና ኮሌጁን አጠቃላይ አካዳሚያዊና የምርምር ሥራዎችን በሚመለከት የውሳኔ ሀሳቦችን አዘጋጅቶ ለዋና ዳይረክቴሩ ያቀርባል፣
2) የህክምና ኮሌጁን አካዳሚክ ካላንደር አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፀድቅለትም አፈፃፀሙን ይመራል፣
3) የየትምህርት ክፍሎች ሀላፊዎች በትምህርት ክፍሎች መምህራን

qixxeesse shiqishanno, kaajjitusiro jeefishsha massagganno;

3) Rosu golla sooreeyye rosu kifilla rosiisaanonni doorantanno gede assanno;
4) Xinxallote hedo garimma gumulate dooranno. Doortinore lainohunni gumulote hedo qixxeessite qaru dayrekterchira shiqishshanno;
5) Kaajjitino xiinxaawote loossa mixantanno gedenna minxirono jeefishsha qineessanno;
6) Dagoomu owaante handaara aliidimate massaganno;
7) Rosunna qajeelshu kifilla woyyeesatenna dhabachishate loossa loosanno;
8) Rooridi loosu yannasi urrinshu loossara hosiisanno, owanteteno garimma noosi aganu baatooshshenna addi addi horo afiranno;
9) Qaru dayrekterchinni aamantanno woloota loossano loosanno.

**30. <u>Gashshootunna Latishshu Layinki Qara Dayrektoreete Biilloonyenna Loossa</u>**

1) Xagishshu kolleejje lossatenna owaantete gafa halashshate faanshoonni loossa aliiddimmatenni qineessanno;
2) Xagishshu kolleejje gashshootunna mannu wolqa hajubba aliidimmatenni massaganno;
3) Xagishshu kolleejje baalante gashshootunna latishshu handaarrara hasiissannota mannu wolqa batinye lainohunni gumulote hedo qixxeesse qaru dayirekiterichira shiqishanno kaajjiturono seeru garinni loosu aana hosiisanno;
4) Akadamikitenna xagishshu owaante loossa jefisiisate ka’litanno irkote loossa aliidimatenni qineessanno;

እንዲመረጡ ያደርጋል፣

4) የምርምር ሀሳቦች ተገቢነትን በመወሰን ይመርጣል፡፡ የመረጣቸውንም በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለዋና ዳይረክተሩ ያቀርባል፣
5) የፀደቁ የምርምር ስራዎች እንዲታቀዱና ከታቀዱም አፈፃፀማቸውን ያስተባብራል፣
6) የማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍን በበላይነት ይመራል፣
7) የትምህርትና ስልጠና ክፍሎችን የማሻሻያ እና የማጎልበቻ ስራዎችን ያከናውናል፣
8) አብዛኛውን የስራ ጊዜውን ለተቋሙ ስራዎች ያውላል፤ ለአገልግሎቱ ተገቢውን ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅሞች ያገኛል፣
9) በዋና ዳይረክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

**30. <u>አስተዳደር እና ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስልጣንና ተግባር</u>**

1) የህክምና ኮሌጁን ለማሳደግና የአገልግሎት አድማሱን ለማስፋት የታለሙ ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣
2) የህክምና ኮሌጁን አስተዳደራዊና የሰው ሀይል ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል፣
3) ለህክምና ኮሌጁ አሰደተዳደርና ልማት ዘርፎች የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ብዛት በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል ሲፀድቅም በህግ አግባብ መሰረት ይፈፅማል፣
4) አካዳሚክ እና የህክምና አገልግሎት ተግባሮችን ለማሳካት የሚያግዙ ድጋፍ ሰጪ ስራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣
5) ለተማሪዎች እና ለህክምና አገልግሎት የሚያስፈልጉ አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፣

5) Rosaanotenna xagishshu owaantera hasiissanno shiqisho wo’mitanno gede assanno;
6) Xagishshu kolleejje keeraanchimma agarate jironna jajja garunni loosu aana hosiisaate dandiissisanno loossa loosanno;
7) Akkaadaamiketenna xagishshu owaante loosaasine lainohunni deerru lophonna ogimmate horo lainohunni fultanno biddissubbanna gumulo jeefantanno gede assanno;
8) Eonna fulo garimma noonsa faynaansete seeruba garinni millissanno gede assanno;
9) Rooridi yannasi urrinshshu loossara hosiisanno, owanteteno garimma noose aganu batooshshenna horo afi’ranno;
